# ሰርቫንቲስ

## ዶን ኪሾት

### ክፍል አንድ


በሚካኤል ደ ሰርቫንቴስ ሳቬንድራ

1547—1616


ከእስፓንኛ ወደ እንግሊዘኛ

ከሳሙኤል ፑትናም

ከእንግሊዝኛ ወደ አማርኛ

አሰፋው ተፈራ ወ/መስቀል


ግንቦት 1977

| | | | ገጽ |
|---|---|---|---|
| 17. | ምዕራፍ 15 | ዶን ኪሾት እርሀራሄ ከሌላቸው ያንጓሶች ጋር ........................ | 191 |
| 18. | ምዕራፍ 16 | ብልሁ መኰንን ፈረሰኛው ዶን ኪሾት እሱ የመስፍን ግንብ ብሎ ከሰየመው ሆቴል ውስጥ .............. | 204 |
| 19. | ምዕራፍ 17 | ቆፍጣናው ዶን ኪሾት ........... | 217 |
| 20. | ምዕራፍ 18 | በጌትየው በዶን ኪሾትና በጋሻ ጃግሬው በሳንቾ ፓንቻ መካከል የተደረገው አስደሳች ንግግር .............. | 233 |
| 21. | ምዕራፍ 19 | ዶን ኪሾት ከጋሻ ጃግሬው ጋር በጨለማ ሲጓዝ ካንድ ሬሳ ጋር ተገናኝቶ ያከናወነው ግጥሚያ .......... | 252 |
| 22. | ምዕራፍ 20 | በስመ ጥሩነታቸው በመላው ዓለም ላይ የገነኑት ዙዋሪ ፈረሰኞች ...... | 267 |


## ለልዑል ጌታዬ የቬዥር መስፍን

የጂብራሌዎን ማርኪዝ ፣ የቤናልካዛርና የባናሬስ ካውንት ፣ የአልኮሴር አውራጃ ቪስ ካውንት ፣ የካፒላ—የኩሪየል—የቡርጊሎስ ከተማዎች ጋቲዎ ጌታ

ልዑል ጌታዬ ሆይ !

ብልህና አስተዋይ ልዑል እንደመሆንዎ መጠን ማናቸውንም ዓይነት ሥነ ጽሑፍ በቅን አስተያየት እየገመቱ ለመዘክርነት ለመቀበል እጅግ የሚወዱንና የሚፈቅዱ መሆንዎን አጣርቼ ስለማውቅ ፣ ይህን የብልህነትንና የጥሩ ስሜትን ጥበብ የሚገልጥ በተለይም እነዚያ በትውልዳቸው መሠረተ ጨዋነት እየተመኩ ለተራ ጥቅም ዝቅ ብለው ማገልገልን ከታላቅ ውርደት የሚቆጥሩት ልበ ኩሩ ሰዎች የተከተሉትን የሕይወት ጐዳና የሚያብራራ ልብ ወለድ ድርሰት አዘጋጅቼ ለሕዝብ ለማበርከት በጋለ ትጋት ደክሜ ያጠናቀቅሁትን «የባለሞያው መኰንን የማንቻው ዶን ኪሾትን» የሕይወት ታሪክ በልዑልነትዎ ከፍተኛ ጠባቂነት ሥር ለማሳተም ቁርጥ ሀሳብ አደረግሁኝ ።

ይህን ያህላል ተብሎ ለማይገመተው ለልዑልነትዎ ታላቅ ሰውነት የሚገባውን የላቀ ክበሬታ እየሰጠሁ ፣ የልዑልነትዎ መልካም ፈቃድ ሆኖ መጽሐፉን በጥበቃው ሥር እንዲቀበሉኝ እፊትዎ ተንበርክኬ ልመናዬን በፍጹም ትሕትና አቀርባለሁ ።

ይህም መጽሐፍ በልዑልነትዎ ጥላ ሥር የተጠበቀ እንደሆነ ምንም እንኳ በታላላቆቹ ጠቢባን ደራሲዎች ዘንድ የሚዘጋጁት ከፍተኛ ድርሰቶች ሁሉ የሚጐናጸፉትን ዓይነት እጅግ ብርቅና ድንቅ የሆኑትን የለዛ ማጌጫዎችና የመምህርነት ቃላት ያልተጐናጸፈ ደሀ መሆኑን ባውቅ የድንቁርናቸውን ወሰን ሳያከብሩ ጥሰው እያለፉ በሌሎቹ ድካም የተዘጋጀውን ድርሰት ለመንቀፍና ለማኳሰስ ሲሉ በከረረ ጥላቻና በታወረ አስተያየት እየወነጀሉ ሊያጠፉት ከሚነሱት ተንኰለኞች ሊድን ስለሚችል ፣ በዚሁ መጽሐፍ ላይ ጥፋት አይተናል በማለት በምቀኝነት መን

ፈስ እየዶለቱ አስመስለው ለማሳመን አንዳንድ] ሐሳዊ መስካሪ ዎች የሚያቀርቡትን ሐሰተኛ ሰበብ በመቃወም ልዑልነትዎ እርግጠኛና ቁርጠኛ በሆነ ፍርድ ጋሻና ጠበቃ ሆነው ጠላቶ ቹን እንዲከላከሉለት በልዑልነትዎ ተማጥኜአለሁ ።

ስለዚህ የልዑልነትዎ ልበ ብሩህነትና አስተዋይነት የኔን መልካም ስሜት በቅን አስተያየት እንደሚገምቱው ብርቱ እም ነት ስላለኝ ይህችን አነስተኛ-ስጦታ የማበረክተው በአነስተኛ ነቷ ቅር እንዳማይሰኙ ፍጹም እርግጠኛ ሆኜ ነው ።

የልዑልነትዎ ፍጹም ታማኝ አገልጋይ
ሚካኤል ዲ ሰርቫንቴስ ሳቬንድራ



# መግቢያ

## በደራሲው ሕይወት ዙሪያ የተገኘ አጭር ታሪክ

ሚካኤል ሰርቫንቴስ ሳቬንድራ እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በጥቅምት ወር 1547 ዓ. ም. አልካላ ዲ ሔናሬስ ከሚባል አገር ሀብት ከሌላቸው ከምግባረ መልካም ቤተሰብ ወገን ተወለደ ። እርሱ እራሱ እንደተረከው ከልጅነቱ ዕድሜው ጀምሮ መንፈሱን ወደ ቅኔ ትምህርት ማዘንበሉን ብቻ ይገልጻል ፤ ከዚህ በስተቀር በጐልማሳነቱ ዘመን ያሳለፈውን ሁኔታ የሚገልጽ አንድም የታ ሪክ ምንጭ አልተገኘም ።

የመጀመሪያ ትምህርቱን በሳላማንካ ዩኒቨርሲቲ ካስመረቀ በኋላ ቀጥሎ በ1568 ዓ. ም. ወደ ማድሪድ ተዛውሮ ሲማር ከብ ፁዕ ካርዲናል አኳቪቫ ጋር ተዋወቀ ። ብፁዕነታቸውም የወጣ ቱን ብልህነትና ንቃት ተመልክተው ፍቅራቸውን አሳደሩበት ።

ሚካኤል ከብፁዕነታቸው ጋር መተዋወቁን ከታላቅ ዕድል ስለቆጠረው ምኞቱን ለመፈጸም ሲል በእልፍኝ አሽከርነት ደንብ አድሮላቸው ተከትሎአቸው ወደ ሮም ለመሄድ ቁርጥ አሳብ አደረገ ። ይህን የመሰለው የአገልግሎት ደንብ ባንድ የቤተ ክህነት ወራሴ መንበር ዘንድ እንደማናቸውም ተራ አሽከርነት የሚቆጠር ሥራ አልነበረምና ሚካኤል ከብፁዕነታቸው ጋር በቆየበት ጊዜያት ማናቸውም መልካም አያያዝና ባለሟል ነት አልተጓደለበትም ነበር ። ይልቁንም በዚያን ዘመን በእስፓ ኒያ አገር በአኗኗራቸው እጅግ ተግደርዳሪ ከነበሩት የጨዋ ልጆ ችና ዛሬ በዘመኑ መለወጥ የተነሳ የጥንት ክብራቸውን አጥተው ድህነት ከተጫናቸው ወገኖች የሮምን ከተማ ጥንታዊ ታሪክና ውበት ለመጐብኘትና እንዲሁም የተፈጥሮ ስጦታቸውን በትም ህርት ለማሻሻል ከሚመኙት ወጣቶች መካከል አንደኛው ሚካ ኤል ስለነበረ የጀመረውን ትምህርት አቋርጦ ወደ ሮም ለመ ሄድ በመነሳቱ ቅር አልተሰኘም ነበር ። ሮምም በሚገኝበት ጊዜ እንደተመለከተው ተስፋው የተመሠረተበት የወደፊት ምኞቱ

ማግባት የተሻለ መሆኑን ስለመረጠ የአምስት መቶ ወቄት ወርቅ ጌታ ነበርና ዋጋውን ለመጀመሪያ ጌታው ለአርናውቴ ማሚ እጅ በጅ ከፍሎ በባርነት ገዛው ።

ይህን የመሰለ የመከራ ቀንበር በሚካኤል ጫንቃ ላይ መውደቁን የሰርቫንቲስ ቤተሰቦች ስለሰሙ እርሱን ከባርነት ነጻ ለማውጣት የሚከፈል የወጆ ገንዘብ መራር በሆነ ችግር ማጠራቀም ጀመሩ ። በዚያኑ ዘመን ሚካኤል ስለርሱና ስለክርስቲያን ወገኖቹ ነጻነት የሚያደርገው ትግል ዘወትር መሰናክል እያገኘው ተዳክሞ ነበርና በትግሉ መክሸፍ የተቆረቆሩት የእስፓኒያ ሕዝቦች እነዚያን በአልጄር ግዛት ውስጥ በባርነት የሚገዙትን ክርስቲያናት በሚቻላቸው መንገድ ነጻ ለማውጣት የሚረዳቸውን ዘዴ ለመፈለግ ሲሉ ተሰብስበው ከተማከሩ በኋላ«የቅድስት ሥላሴ መነኰሳት ማኅበር» የተባለ አንድ ሚሲዮን በሕዝቡ መዋጮና ዕርዳታ አቋቋሙ ።

የሰርቫንቲስ ቤተሰቦች በተለይ ለወጆ ያጠራቀሙትን ገንዘብ ለልጃቸው ነጻነት ዋጋ እንዲከፈል ለሚሲዮን አለቃ አስረከቡና ወዲያውኑ በግንቦት ወር 1580 ዓ. ም. ላይ ሚሲዮናውያኖቹ አልጄር ግዛት ገብተው ስለባሪያ ነጻነት የሚደረገውን የመግባቢያ ውል መነጋገር ጀመሩ ። አረመኔው ሐሰን አጋ ግን የውሉን ሐሳብ ሲቀበል በተለይ ሚካኤልን ነጻ ለመልቀቅ የጠየቀው ገንዘብ የገዛበትን እጥፍ ስለሆነ እሱን ነጻ ለማውጣት ያጋጠመ ችግር የማይዘለቅ መስሎ ነበር ። ነገር ግን መችም የማይቀር ዕዳ በመሆኑ አባ ጄል የሚባሉት የሚሲዮን አለቃ በጉዳዩ ከተጨነቁበት በኋላ ከማኅበሩ ስንቅ ላይ አምስት መቶ ወቄት ወርቅ ጨምረው ከብዙ ልመና ጋር አንድ ሺህ ወቄት ወርቅ ከፍለው ባላባቱን ለማስደሰት ቻሉ ።

እንዳጋጣሚ የዚያኑ ዕለት ሚካኤል ወደ ቱርክ አገር ተሻግሮ ለመሸጥ ከሌሎች ጋር በሰንሰለት ተቆራኝቶ ወደ ኰስታንቲኖፕል ለመጓዝ ተዘጋጅቶ ከወደቡ ላይ ከሚገኘው መርከብ ውስጥ ተሣፍሮ ስለነበረ ዋጋው ከተከፈለ በኋላ ከሌሎቹ እሥረኞች መጨረሻ ወርዶ እጁ ለሚሲዮኑ አለቃ ተሰጠ ።



ከዚያ ወዲህ አገሩ ገብቶ ከቤተሰቦቹ ጋር ተቀላቅሎ ሲኖር የአዞሮች ዘመቻ በተደረገ ጊዜ እንደገና በሶስተኛው ክፍለ ጦር ውስጥ አባል ሆኖ እስከ 1583 ዓ. ም. ድረስ በወታደርነት አገልግሏል ። በ1584 ዓ. ም. ካቴሪና ፖላቼዎስ ኢ. ሳላዛር የምትባል ትውልዷ ከጨዋ ወገን ሆኖ በአኗኗሯ እንደ ተራ ሰው ደሀ የሆነች ልጅ አግብቶ ትዳር ከያዘ በኋላ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የወታደርነት ተግባሩን አቋርጦ መተዳደሪያውን በጽሕፈት ሥራ ላይ መሠረተ ።

ለመጀመሪያ ጊዜ «ጋላቴያ» (የመልካም አስተዳደግ ምክር) ብሎ የሰየመውን የእረኞች የተረት መጽሐፍ ጻፈ ። ከሱም ቀጥሎ በሰው ልጅ ላይ የሚታየውን ጉልህ ስህተትና እንዲሁም ልማድን በመከተል የሚደርስበት የድንቁርና እምነት ሁሉ ለሥልጣኔና ለአእምሮ እድገት ጠንቀኛ ደዌ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ፤ ከተፈጥሮ ስጦታ ፈልቀው የተዘጋጁ ፤ ብሩህ የሆነ የሐሳብ አገላለጥ ያላቸው እያሌ መጻሕፍት ጽፎ ነበር ። ነገር ግን በዘመኑ ቤተ መጻሕፍት ባለመጠበቃቸው የተነሳ ሁሉም በጊዜ ብዛት እየባከኑ ጠፍተዋል ።

ሚካኤል ሰርቫንቲስ በጽሕፈት ሥራ ተወስኖ ሲኖር ብዕሩ ማለት የጸሐፊነት ሞያው ኑሮውን የሚደግፍበት በቂ ጥቅም የማያፈራለት መሆኑን ስለተረዳው ይህን ሥራ ትቶ ሌላ የተሻለ ጥቅም የሚገኝበት ሥራ መፈለግ ግዴታ ሆነበት ። ስለዚህ ያለፈውን የወታደርነት አገልግሎቱን በማስታወስ የሥራ ጥያቄ ማመልከቻውን ለባለሥልጣናቱ ቢያቀርብ ለጊዜው ሊሰጡት የቻሉት ሥራ በመርከብ ወደ ሲቪሊያ ለሚመላለሱት ለሕንድ ነጋዴዎች ወጭ ሸቀጥ ማቅረብና ገቢ የንግድ ዕቃ መቆጣጠር ነበር ። ይህም ሥራ ወዲያው በ1592 ዓ. ም. ግድም ስለቆመ ወደ ማዘጋጃ ቤት ተዛውሮ ። ከሕዝብ ጥቅም ገቢና ከሥራ ማኅበር ቀረጥ በመቀበል ሥራ ተቀጥሮ ከቀድሞው ደረጃው ቁል ቁል ወርዶ ተገኘ ። ይህንንም ሥራ ለጥቂት ጊዜ ከሠራ በኋላ በብስጭት ምክንያት ትቶ ወደ እንዳሉሲያ ሄዶ ተቀመጠ ። እዚያም በነበረበት ሰሞን እጅግ የጣመና የተመሰገነ ልዩ ልዩ የተረትና የምሳሌ መጽሐፍ ጽፎ ለሕዝብ አበረከተ ።

ባብ ስላስገደደው ብዙ በማንበቡና የብዙ ጊዜ እንቅልፍ በማጣቱ ምክንያት አንጎሉ ስለደረቀ ልቡን እንደመንሳት አድርጎት ስነበተና በመጨረሻው አሳበደው ።

አስተያየቱ ሁሉ በየድርሰቶቹ ገጽ ተጽፈው ባነበባቸው ታሪኮች ታጨቀ ። ማመዛዘንና በትክክል መፍረድ እንዳይችል አእምሮው ተናጋበት ። ዘወትር የሚታየው ሁሉ የአስማትና የምትሐት ጥበብ ፣ ጠብ መጫር ፣ መፎካከርና መዛዛት ፣ ፣ውጊያ መግጠምና መቁሰል ፣ ጉራ መንዛት ፣ ፍቅር መወጠን ፣ በልብ ኩራት ማሳደርና እንዲሁም እጅግ ብርቱና አደገኛ የሆኑትን ተግባሮች ፈጽሞ ለመገኘት መጣጣር፣ እነዚህንና ሌላም ዝብርቅርቅ ያሉ አታካችና ፍሬ ቢስ ሁኔታዎች ተዋህደውት ከቀናው መንገድ እንዲወጣ አደረጉት ።

እነዚህም የቅዠት ትርኢቶችና ፈጠራዎች ሁሉ በደራያን አሳቢነት የተጻፉና ስለጥንታውያን ፈረሰኞች ሞያ የሚናገሩ ልብ ወለድ ታሪኮች ከመሆናቸው በቀር እውነተኛ ድርጊቶች ስላልነበሩ ዶን ኪሾት በተመራመረው መጠን ይህ ተደረገ ተብሎ የተወራው ታሪክ ሁሉ ንጹሕ እውነት መሆኑን አምኖ ለመቀበል እስኪሸነፍ ድረስ በአእምሮው ውስጥ ስለጠቀጠቀው በሱ ግምት በዓለም ላይ ከዚህ ይበልጥ እውነተኛ የሆነ ታሪክ አለመኖሩን አረጋገጠ ። እሱም በበኩሉ ታሪኩን በመደገፍና በማረም አስተያየቱን ሲሰጥ «ሰይድ ሩዋይ ዲያዝ የሚባለው ጀግና ያለጥርጥር ምርጥ ፈረሰኛ ነበር ፣ ይሁን እንጂ ከባለ አብረቅራቂው ሠይፍ ፈረሰኛ ጋር ሊወዳደር የሚችል አልነበረም ፣ ይኸኛው ከሁለት ኃይለኞች ከሆኑ ሰማይ ጠቀስ ጃዊማዎች ጋር ተጋጥመው ባንድ የሠይፍ ስንዘራ ብቻ አካላቸውን መሐል ለመሐል ስለተረከካቸው ጀግንነቱ ከፍ ያለ ብልጫ አግኝቷል» ።

«ከሱ የሚበልጥ ጀግና ለማግኘት የተፈለገ እንደሆን ግን» ቤርናርዶ ዲካርፒዮ የሚባለው»የሚያይል ነው ። ይህም ፈረሰኛ በድፍረትና በቆራጥነት የተዳኘውን ሮናልዶ የሚባለውን ፈረሰኛ ሮንቺስቫሌ ላይ ገድሎታል ። አገዳደሉም ጃውማው ኤር



ኩሌ የምድርን ልጅ አንቴዎን እግሩን ከመሬት አላቅቆ በእጁ እንገቱን አንቆ በገደለበት አኳኋን በዚሁ ብልሃት ተጠቅሞ ነው ። ከዚህ በስተቀር ደግሞ ስለጀግናው ሞርጋንቴ የትህትና ጠባይ ደራሲው የተናገረው ሁሉ እጅግ ከፍ ያለ ምሥጋና የሚያስጠው ነው ። ምክንያቱም እሱ ብቻ ከሌሎቹ በተፈጥሮ ጠባያቸው ትእቢተኞችና ሰው ናቂዎች ከሆኑት ጃዊማዎች በማይገጥም አኳኋን አመለ ጌታና ሰው አክባሪ አኩሪ ትሁት ግብረገብ ሰው ነበረ። እንዲሁም ከነዚህ ሁሉ በላይ በስመ ገናናነቱ ጎልቶ የሚታየው ሬናልዶ ዴ. ሞንቴአልባኖ ነው ። በተለይም ከመኖሪያ ግንቡ በወጣ ጊዜ ከፊቱ ያገኛቸውን ሰዎች ሁሉ በጎራዴ እየጨፈጨፈ እንደ ቅጠል እያራገፋቸው ጥሶ በማለፉና በታሪኩም ላይ እንደሚተረከው ሁለመናው በወርቅ የተሠራውን የመሐመድን ሐውልት በሠረቀ ጊዜ ታምራዊ ድፍረት በማሳየቱ እንደ ፀሐይ በምድር ላይ ሲያበራ የሚኖር ዝና ተቀዳጅቷል» ። እያለ በመቀጠል ሲተች ቆየና ወደ ከሃዲው የማጋንሳው ጋኖ ታሪክ ላይ ስለደረሰ በሰውየው ጅላጅልነትና እንከፍነት ተናዶ ከፊቱ ያገኘው መስሎት በእርግጫ ሊፈነችረው እግሩን ሲሰነዝር በመሳሳት አሮጊቷንና የወንድሙን ልጅ ሊደርባቸው ነበር ።

በዚህ መንፈስ ተነኳልሎ አንጎሉ ፈጽሞ ስለወደመ ያንድ የለየለት ዕብድ አእምሮ እንኳ ይሠራዋል ተብሎ የማይታሰበውን የቅሌት ሥራ ለመሥራት ታጥቆ ተነሣ ። ዓላማውም የራሱን ክብር ለማሳደግም ሆነ ለዓለም ቤዛ ለመሆን ዙዋሪ ፈረሰኛ ሆኖ ፣ የጦር መሣሪያ ይዞ በፈረስ ላይ ተቀምጦ ዓለምን እየዞረ አጋጣሚውን መፈለግና እንዲሁም በታሪክ ላይ አንብቦ እንደ ተረዳው ሁሉ ዙዋሪ ፈረሰኞች ለአደጋ በሚጋፈጡበት ዓይነትና አኳኋን እሱም ለማናቸውም አደጋ አልፎ እየተጋፈጠ የሕዝቡን ሠላማዊ ኑሮ ለማናጋት ባንዳንድ ትምክህተኞች ጥጋብ የሚፈጸሙትን የግፍ ሥራዎች ለመበቀል ፣ ለአደጋ በመከለልና ከወደረኛው ጋር እየተዋጋ በአሸናፊነት የዘለቀ እንደሆነ ደካማዎችን ለመርዳት ሲል ባደረገው ተጋድሎ ዘላለማዊ ክብርና ምሥጋና ገብይቶ የማይሞት ስም ለማትረፍ ነበር ። የራሱን ክብር ማሳደግ ብቻ ሳይሆን ብሔራዊ ተግባሩ እንደሆነ ይቆጥረው ነበር ።

ይህ ምስኪን ሰው ለከንዱ ብርታት ምሥጋና ይድረሰውና ይህን የወደፊት ተግባሩን አፈጻጸም በሚያሰላስልበት ጊዜ በትንቢት ምኞቱ ዘውድ ጭኖ ቢያንስ ቢያንስ የትሬቢዞንዳ ንጉሠ ነገሥት መሆኑ እንደሕልም ይታየው ነበር ። በዚህ ከንቱ ተስፋ እየተገፋፋና ከተስፋውም ያገኘው ደስታ እያጠገበው ለተወራው የፈረሰኛነት ተግባር ብርቱ ፍቅር ስላደረበት ፍላጎቱን ወደ ፍጻሜ የሚያደርስበትን አቅድ ከሥራ ሊያውል ይጣደፍ ጀመር ።

ከሁሉ አስቀድሞ ለተግባሩ ማከናወኛ የሚገለገልባቸው በያይነቱ የጦር መሣሪያዎች ማግኘት አስፈላጊው መሆኑ ትዝ ስላለው የቅድማያቶቹ ቅርስ የነበሩ ፥ ከብዙ መቶ ዓመታት ጀምሮ በቤቱ ባንዱ ጥግ ተረስተው የተቀመጡ የዛጉና የሻገቱ መሣሪያዎች መጠራረግ ጀመረ ።ዝገቱን እየፈቀፈቀ አስለቅቆ ቅባት ቀባብቶ የተቻለውን ያህል ካጸዳቸው በኋላ ባንዳኛው መሣሪያ ላይ በጣም ጠቃሚ የሆነው ወገን የሚጎድለው መሆኑን ተመለከተ ። ይህም አንድ መናኛ ተራ የእራስ ቆብ እንጂ ፊቱን በሙሉ የሚሸፍን ደንበኛ የራስ ቁር አልነበረም፤ ነገር ግን በጉድለቱ ተስፋ መቁረጥ የማይገባ መሆኑን በመረዳት በገዛ ብልሀቱ ፈጥሮ ወፈር ያለ የወረቀት ክርታስ በልኩ ከርክሞ በዚያ በጎደለው ቦታ እየሸጎጠ ጠጋግነውና ለጊዜው ደንበኛ የራስ ቁር አስመስሎ አበጀው ።

ነገር ግን በቅርብ ጊዜ በሚጀምረው የውጊያ ተግባሩ ላይ የሚገጥመውን የጐራዴ ምት ለመመከት የራስ ቁሩ በቂ ጥንካሬ ያለው መሆኑን ለመፈተን ስለፈለገ ፥ እመሬት ላይ አስቀመጠና ጐራዴውን መዝዞ ሁለት ጊዜ መታው ። ዳሩ ግን ይህ የመጀመሪያው ምት ብቻ ሳምንት ሙሉ የተደከመበትን ሥራ ባንድ አፍታ ሊበታትነው ቻለ ። የዚህ ራስ ቁር በቀላሉ መነካካት የሥራውን ግብዝነት ስለመሰከረበት እንደገና አጠናክሮ ለመሥራትና ከማናቸውም አደጋ የተረጋገጠ ለመሆን ሲል በክርታሱ ፈንታ ቀጭን የብረት ሽቦ ጣልቃ እያገባ አፍረግርጎ በጥንካሬውና ባሠራሩ ከመጀመሪያ የተሻለ አድርጎ ጠጋገነው ። ከዚህ በኋላ ሌላ ቄንጥና ማሳመር ሳያበዛ መናኛውን የራስ ቆብ ደንበኛ የራስ ቁር አድርጎ ለወጠው ።



ቀጥሎም ፈረሱን ለመጎብኘት ወደ ታሠረበት ጋጣ ፈጥኖ ሄደ ፥ ምንም እንኳ ይህ ያልታደለ ፈረስ ያረጀና የደከመ ፥ እጥንትና ጠጉር ብቻ የቀረው ከነጋዴ አጋሰስ ይበልጥ የተገጠበ ጌኛ ቢሆንም በርሱ የዕብደት አስተያየት የዓለምን ፈረሶች በተለይም የእስክንድርን ቡቄፋሎስና የሰይድን ባቢዮካ በጮሌነት እንደሚበልጣቸው ይተማመንበት ነበርና በትምክህት ዓይን አንገቱን እየተመተመ ፥ ጋማውን እያሻሸ አባብሶት ተመለሰ ።

ፈረሱም ከዚህ ቀደም የመጠሪያ ስም ስላልነበረው ወደፊት የሚያወጣለትን ስም አራት ቀን ሙሉ ሲፈልግ ሰነበተ። ስም ለማውጣት ያሰበበትም ዋናው ምክንያት አንድ ስመ ጥር ፈረሰኛ የሚቀመጥበት ፈረስ በዓለም ላይ የታወቀ ያለ ስም እንዲኖር አስፈላጊና የተገባ አለ መሆኑን ባነበበው ታሪክ ላይ ከተረዳው በኋላ ነው ። እንዲሁም ደግሞ ጌታው የቀድሞ ተግባሩን በሚለውጥበት ጊዜ የፈረሱም ሁኔታ አብሮ መለወጥ ከጥንት የቆየ የፈረሰኞች ልምድ ስለሆነ ጌታውና ፈረሱ በቅርብ ጊዜ አብረው ለሚጀምሩት ለዚህ እጅግ ከፍ ላለውና ለገነነው የፈረሰኛነት ተግባር መመኪያና መኩሪያ መሆኑን የሚያረጋግጥና እንዲሁም ያንድ ዙዋሪ ፈረሰኛ ምግሳዊ ፈረስ ከመሆኑ በፊት ምን እንደነበረና አሁን ደግሞ ወደ የትኛው ደረጃ ለመድረስ እንደተቃረበ የሚያስረዳ ጥሩ ስም ሳያወጣለት መቅረቱ የተገባ አለመሆኑን ስለተገነዘበው ነው ።

በዚህ አኳኋን በቅገርት መንፈሱ ሲያወጣና ሲያወርድ ፤ ሲመርጥና ፥ ሲለውጥ ሲያስረዝምና ሲያሳጥር ፤ ሰንብቶ በመጨረሻው «ሮዚናንቴ» የተባለውን ስም በመስጠት ተወሰነ ። ይህም ስም በራሱ ግምት እጅግ የላቀና የተብራራ ትርጉም ያለው መሆኑን አመነ ። ምክንያቱም «ሮዚኖ» የተባለው ፈረስ በጥንት ዘመን በመላው ዓለም በጋላቢነት ሞያው የተመሰገነ መሆኑን በታሪክ ላይ ተረድቶት ስለነበረ ባደረገው ምርጫ ቅር አልተሰኘበትም ነበር ።

ይህን መልካም ስም ለፈረሱ ከሰጠ በኋላ ለራሱ ደግሞ አንድ የሚያኰራ ስም መፈለግ ጀመረ ። ነገር ግን ለራሱ የሚ

ችን ጨርሶ የሌለ በመሆኑ ልናገኝልዎ ባለመቻላችን እናዝና
ለን» አለው ።

ዶን ኪሾትም ይህ «ከምሽጉ ገዥ» ሆቴለኛውንና ሆቴሉን
እንዲህ ብሎ ሰይሞአቸዋልና የቀረበለት የከበሬታና የትህትና
አቀባበል በጣም ስላስደሰተው እንዲህ ሲል በጉራ አነጋገር
መለሰለት ፤

«እጅግ የተከበሩ የግንቡ ገዥ ሆይ! ድንገተኛ ለሆነው እን
ግድነቴ አቀባበል እስከዚህ ድረስ ተጨንቀው ስላሰቡልኝ ከልብ
አመሰግንዎታለሁ ። ዳሩ ግን የፈረሰኛነት ተግባሬ ማናቸውንም
ዓይነት ድሎት የማይጠይቅ ስለሆነ ምቾት ያለው መስተንግዶ
እንዲያደርጉልኝ አላሳሰብዎትም ። ምክንያቱም የፈረሰኛነት
ምኞቴና ጌጤ ይህ የታጠቅሁት መሣሪያዬ ስለሆነና እረፍቴም
የዘወትር ውጊያና አደጋን ማሳደድ ስለሆነ ነው» አለው ።

ሆቴለኛው ግን «የግንቡ መስፍን (ካስቲላኖ) ብሎ ሲጠራው
በሰማው ጊዜ በሌላ አጠራር ተረጉመውና » ይህ ሰው ካስቴ
ላኖ ማለቱ የካስቴሌያ የጨዋ ልጅ መስየው ይሆናል ሲል
አሰበ ። እሱ ግን ልቦናው እንደሚያውቀው ያንዳሉሲያ አገር
ተወላጅ ነበር ፤ እንዲያውም በተለይ ከእንዳሉሲያ ውስጥ ከቅ
ዱስ ሉካር አውራጃ ባላገሮች የሚወለድ ሌብነታቸው እን
ደካኩ ከሆኑት መካከል አንዱ ነበርና በበኩሉ እንዲህ ሲል
መልሱን ሰጠው ። ክቡርነትዎ በመረጡት ዓይነት መኝታዎን
በሚጐረብጥ ኮረት ላይ እናነጥፍልዎታለን ፤ እንቅልፍዎም
ዘወትር መንቃት ይሆናል ። ስለዚህ በሆቴላችን ውስጥ አንድ
ሌሊት ብቻ ሳይሆን ያመቱን ለሊቶች በሙሉ እንቅልፍና ጸጥታ
የሚነሳ ጫጫታ ስላለ ዓመቱን በሙሉ እንደነቁ ለመገኘት የሚ
ያስችልዎ ምክንያት መኖሩን አረጋግጠው ከፈረስዎ ላይ ለመ
ውረድ ይችላሉ» አለው ።

ይህን ተናግሮ ሲያበቃ ወዲያውኑ እርካቡን ሊይዝለት አጐ
ነበሰ ። ዶን ኪሾትም ቀኑን በሙሉ አንዲት ጉርሻ ምግብ
እንኳ ሳይቀምስ ጠሙን እንደዋለ ነበረና ብዙ ችግርና ድካም
እንደተጫጫነው ከፈረሱ ላይ ወርዶ ወደሆቴሉ ገባ ። ገብቶም



እንደተቀመጠ ወዲያውኑ የፈረሱን ድካም አስታወሰና ሆቴለ
ኛውን ጠርቶ እንዲህ ሲል አዘዘው ።

«ይህ ፈረስ ከዓለም ፈረሶች ይበልጥ የከበረና ጥሬ በመመ
ገብ ተቀማጥሎ ያደገ ስለሆነ የሚያስፈልገውን መልካም አያያ
ዝና ጥንቃቄ ያድርጉለት» አለው ። ሆቴለኛውም የፈረሱን ሁኔታ
ሲመለከተው ዶን ኪሾት እንደሚለው ሆኖ ስላላገኘውና እንዲ
ያውም እኩሌታውን ያህል እንኳ ስላልገመተው ከመጋጃነት
የተሻለ አስተያየት አልሰጠውም ነበር ። ሆኖም ማኳሰሱን ሳያ
በዛ ወደጋጣ ነድቶ ቦታ ካስያዘው በኋላ እንግዳው የሚሰጠውን
ትእዛዝ ለማስማት ተመለሰ ። በዚህም ጊዜ ዶን ኪሾት ከኮረዳ
ዎቹ ጋር ታርቆ የወዳጅነት ጭውውት ማድረስ ጀምሮ ነበር።
እነሱም ቀድም በመሳቃቸው አስቀይመውት ለነበረው ካሣ
ይሆን ዘንድ ፈረሰኛው ትጥቁን በሚፈታበት ጊዜ መሣሪያውን
እየተቀበሉ በማስቀመጥ ይረዱት ነበር ። መጀመሪያ በትከሻ
ውና በደረቱ ላይ ያለውን የብረት ልብስ ካወለቁለት በኋላ የራስ
ቁሩን ደግሞ ሊያወልቁለት ሞከሩ ። ዳሩ ግን ከጭንቅላቱ እስከ
አገጩ ድረስ ያጠለቀው ቅጥልጥል የራስ ቁር እንደማይወልቅ
አድርጎ ባረንጓዴ ጥብጣብ ተብትቦ አሥሮት ስለነበረ ፣ የአን
ገት ጌውም ቋጠሮ የጠበቀ በመሆኑ ፤ በስንጢ ካልቆረጡት
በስተቀር በፍጹም ለመፍታት የማይችሉት ስለሆነ እሱም እን
ዲቆርጡበት ስላልፈቀደ ፤ በዚህ አኳኋን የራስ ቁሩን እንዳደረገ
ሙሉን ሌሊት ታይቶ የማይታወቅ የአስቂነት መልክ እየጋበዘ
በሆቴሉ የሠፈሩትን እንግዶች ሲያስቅቃቸው አደረ ። እነዚያ
መሣሪያውን በመቀበልና ትጥቁን በመፍታት ሲረዱት የነበሩት
ሁለት ኮረዳዎች የዶን ኪሾት አጫዋችነት በጣም ስላስደሰታቸው
ካጠገቡ አልራቁም ነበርና ዶን ኪሾት በቀዠባሪነቱ እንደገመ
ታቸው በዚህ የመስፍን ግንብ ውስጥ በመጀመሪያ የክብር ደረጃ
ላይ የሚገኙ እመቤታትና ወይዛዝራት መሆናቸውን በማመን
ልብ በሚነካ ዜማ እያንጐራጐረ ቀጥሎ ያለውን ግጥም ያሰማ
ቸው ጀመር ።

በክብር አወዳድረው እንደ ዶን ኪሾት ፣
ወይዛዝርት በሥርዓት እያገለገሉት ፣

ያለው እስከ ዛሬ ድረስ በፈረሰኛነት ሕግ ውስጥ ጋሻ ጃግሬዎች
እንዳያቃስቱ የሚከለክል አንድም አንቀጽ አለማንበቡን መሠረት
አድርጎ ነው ። ይሁን እንጂ በሰውነቱ ላይ የደረሰበትን ጉዳት
መቻል አቅቶት በሕግ ወጥነት ሲያቃስት የተሰማ ጋሻ ጃግሬ
ከጌታው የለመደው ይሆናል ተብሎ በሐሜት የሚያስጐሽመው
መሆኑን ሳያስጠነቅቀው ለማለፍ አልፈለገም ነበር ። ንግግራቸው
እዚህ ላይ እንዳለቀ ሳንቾ ቀጠለና የምሳ ሰዓት መድረሱን
ለጌታው አስታወቀ ። ዶን ኪሾት ግን ባሁኑ ሰዓት ምግብ ያላስ
ኘው መሆኑን በመግለጽ እሱ እንዳሰኘውና እንደመሰለው እንዲ
በላ ፈቀደለት ። ሳንቾም ይህን ፈቃድ ካገኘ በኋላ ሌላ ጥያቄና
መግደርደር ሳያበዛ ፤ የተቻለውን ያህል ተደላድሎ አህያው ላይ
ተቀመጠና ከኮሮጆው ውስጥ የከተተውን ዳቦና ደረቅ አይብ
አውጥቶ እየገመጠ ከጌታው ኋላ ይሄድ ጀመር ፤ እየቆየም ስርቅ
ሲይዘው እርኮቱን ወደ አፉ ያዘነብልና የማላጋን ወይን ቀምቃሚ
በሚያስቀና አጠጣጥ እየመጠጠ ይጐነጭ ነበር ፤ በዚህ አኳኋን
አከታትሎ እየጠጣ በሚጓዝበት ጊዜ ጌታው የሰጠውን ታላቁን
የደሴት ገዢነት ተስፋ እንኳ እስከ መርሳት ደርሶ ነበር ።
የቱን ያህል አደገኛም ቢሆን ከቤት ወጥቶ ጫካ ለጫካ ፤ ገጠር
ለገጠር እየተዘዋወረ አጋጣሚን መፈለግ ፈጽሞ ድካም የሌለበ
ትና እንዲያውም እውነተኛው ረፍትና ምቾት የሚገኝበት ጉዞ
መስሎ ታይቶት ነበር ።

ጌታና አሽከር ምንም አዲስ ነገር ሳያጋጥማቸው ብዙ ምዕ
ራፍ መንገድ ከተጓዙ በኋላ ጊዜው ስለጨለመ ከፊት ለፊታ
ቸው በርከት ያሉ ዛፎች ወደሚገኙበት ጫካ ውስጥ ገብተው
ለማደር ወሰኑ ። ዶን ኪሾትም ያንን የቫርጋስን ታሪክ ጠቅሶ
የተናገረውን አስታወሰና አንድ በጦር ፋንታ የሚያገለግለው
ደረቅ ጨፈቃ ገንጥሎ ከዚያ ከተሰበረው ላይ ያወለቀውን የጦር
ስለት አዋደደበት ። የዚያን ዕለት ሌሊት ፈረሰኞችን እንቅልፍ
በፍጹም አሊያዘውም ነበር ፤ ምክንያቱም በዚያ በመጽሐፍ ላይ
ካነበበው ሁኔታ ጋር ለመተካከል ፈልጎ እመቤቱን ዱል ቺኒያን
በልቦናው እያሰበ ትዝታዋን ባይኑ ላይ መቅረጽ ስለተገባው
ነው ። ይህም አደራረግ አያሌ ዙዋሪ ፈረሰኞች ሲያደርጉት እንደ
ነበረው ኃሳባቸውን በቀጥታ በእመቤታቸው ትዝታ ላይ አሳር



ፈው በየጫካውና በየበረሃው በሚዘዋወሩበት ጊዜ ብዙውን ሌሊት
እንቅልፍ ሳይወስዳቸው ዓይናቸውን እንዳፈጠጡ ያነቱ እንደነበር
ተጽፎ የሚገኝ በመሆኑ ነው ። ሳንቾ ፖንቻ ግን ሌሊቱን ያሳ
ለፈው በዚሁ አኳኋን አልነበረም ፤ ምክንያቱም ቀድሞ እንደተነ
ገረው ያንን ከርሱን በውሀና በጐመን ሳይሆን በትኩስ ሥጋ ቅ
ሞልቶት ስለነበር ለመጋደም ከመቻኮሉ በስተቀር የጌታውን ትካ
ዜና ትዝታ ለመካፈል ባለማሰቡ ነው ። ስለዚህ አስቀድሞ አህያ
ይቱን ከግንድ ላይ አሠረና ቅጠል መልምሎ መኝታውን አነጠ
ፈና ጌታውን በትካዜ እንደተጨበጠ ጐልቶት አልፎ ተገነደሰ ።
ገና ጐኑን ከማሳረፉም ወዲያውኑ የወሰደው እንቅልፍ ላንድ
ሳምንት የሚበቃው ነበር ። ሆኖም ነግቶ እስኪረፍድ ድረስ
አልተንቀሳቀሰም ነበርና ጌታው ተናዶ እየረገጠ ጠርቶ ባይቀሰ
ቅሰው ኖሮ በፊቱ ላይ የሚያንፀባርቀው የማለዳ ጮራና የአዲሱን
ቀን መውጣት በምስጋና ለማብሰር ከዛፍ ወደዛፍ እየበረሩ በደ
ስታ የሚንጫጩት አዕዋፎች ዜማ እንኳ ሊያነቃው የሚችል
አልነበረም ። በጉትጐታ ብዛት ባንኖ እንደተነሳ ወዲያውኑ የእራስ
ጌውን እርኮት ዳበሰና ቢንጠው ከትላንትናው ይዞታው በጣም
ጐድሎ ሲንቦጫቦጭ ስለሰማ ይህን ታላቅ ጉድለት በቶሎ ለመ
ሙላት የሚቻልበት ዘዴ በቅርብ ሥፍራ እንደማይገኝ ተረድቶ
ልቡ በፀፀት እስኪነደፍ አዘነ ።

ዶን ኪሾት ግን እስካሁንም ድረስ አልበላም ነበር ፤ ምክ
ያቱም ቀድሞ እንደተናገርነው ጣዕም ያለው ትዝታ እየተመገበ
ልቡ ጠግቦ ስለአደረ ነው ። ስለዚህ እንደወትሮው ልማዱ ገና
ዱሮ ታጥቆ ለመነሳት ዝግጁ ሆኖ ነበር ። ሳንቾም ከነቃ በኋላ
ከመነሳት አልዘገየም ነበር ። ሁለቱም ከብቶቻቸውን ጭነው
ከጫካው ከወጡ በኋላ ወደ ፑዬርቶ ላፒቼ መንገድ ተመልሰው
ጉዞአቸውን ጀመሩ ። ከቀትር በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ግድም ከፊት ለፊ
ታቸው በርከት ያሉ መንገደኞች ወደነሱ ሲመጡ አዩ ።

ዶን ኪሾት ሰዎቹን ከማየቱ ወዲያውኑ እንዲህ አለ ።
«ወዳጄ ሳንቾ እዚህ ሥፍራ ላይ በነዚያ አጋጣሚ በምንላቸው
ውስጥ እጃችንን እስከ ክንዳችን ድረስ ለመንከር እንደምንችል
አረጋግጥልሃለሁ ። ዳሩ ግን አሁን አጥብቄ የማስጠነቅቅህ አንድ

